በአዲስ ክትትል ("ሲድራ") የወጡት የብር ኖቶች ከፍ ያለ የደኅንነት ደረጃ፣ ዘመናዊናትና ተደራሽነት ("ኔጊሹት") የሚያንጸባርቁ ናቸው። የብር ኖቶቹ አንደኛው ከሌላው የሚለዩት በቀለምና በርዝመት ሲሆን በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች የተሠሩ የተራቀቁ የደኅንነት ምልክቶችን ይዘዋል።

ኖቶቹ ለዓይነ ስውራንና የማየት ችግር ላለባቸው ሰዎች ያላቸው ተደራሽነት

ተደራሽነት - አዲሶቹ የብር ኖቶች ከተነደፉ ጊዜ ጀምሮ ለሁሉም የኅብረተሰቡ አካል ያለው ተደራሽነት የእስራኤል ባንክ ዋና ዓላማ ሲሆን ወደፊትም ቢሆን ይህ ጉዳይ ዋነኛ እንደሆነ ይቀጥላል። ባንኩ ለተደራሽነት ካለው አጽንኦት በተለይም የማየት ችግር ላለባቸው አዲሶቹ ኖቶቹ ተደራሽ እንዲሆኑ ካለው መመሪያ አንጻር በውስጣቸው የተለያዩ ነገሮችን አካቷል።

- **በጠርዙ ላይ ያሉ መሥመሮች** - በያንዳንዱ ኖት ላይ ጥንድ መሥመሮች የታተሙ ሲሆን የኖቱ ዋጋ በጨመረ ቁጥር ቁጥራቸው እየጨመረ ይሄዳል።
- **ለያንዳንዱ ኖት የተለያየ ርዝመት** - አዳዲሶቹ ኖቶች በርዝመታቸው የተለያዩ ናቸው። በእያንዳንዱ ኖት መካከል የ7 ሚሊ ሜትር ርዝመት ልዩነት አለ።
- **የኖቱን ዋጋ የሚያመለክቱ ቁጥሮች** - ትላልቅና ጠቆር ያሉ ቁጥሮች በጐላ ቀለም ፈካ ባለ መደብ ላይ የታተሙ ሲሆን ፈካ ያሉ ቁጥሮች ጠቆር ባለ መደብ ላይ ተጽፈዋል።
- **እያንዳንዱ የባንክ ኖት የራሱ የሆነ ገዢ/ጐላ ያለ ቀለም አለው።**

የባንክ ኖቶቹ የሚለወጡበትን ጊዜ አስመልክቶ የወጣ መረጃ

አሁን ጥቅም ላይ ያሉት ኖቶች (የአዲሱ ሼቄል ሴሪ ጋ በሆነው) ለተወሰኑ ዓመታት በሕጋዊ መንገድ ጥቅም ላይ መዋላቸው ይቀጥላል። የድሮ ኖቶች ወደ እስራኤል ባንክ በሚደርሱበት ጊዜ ደረጃ በደረጃ በአዲሶቹ ኖቶች ይቀየራሉ (የአዲሱ ሼቄል ሴሪ ጐ በሆነው)።

ቀጥሎም የእስራኤል ባንክ በሕዝቡ እጅ የሚገኘውን አሮጌውን ኖት በአዲሱ ኖት የሚቀየርበትን መጨረሻ ጊዜ በሚመለከት የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ዝርዝር መመሪያዎችን ያወጣል። እንደዚሁም አሮጌዎቹን ኖቶች በአዲሶቹ መለወጥ ይቻል ዘንድ የተወሰኑ ዓመታት ይመደባሉ።

አዲሱ ባለ200 ሼቄል ኖት

- **ምስል፡** ናታን አልተርማን።
- **ዋናው ደማቁ ቀለም፡** ሰማያዊ።
- **መጠን፡** 150 x 71 ሚሊ ሜትር።
- **የፊት ለፊት ዲዛይን፡** የገጣሚው ምስል በመከር የሚወድቁ ቅጠሎች መደብ ላይ።
- **የጀርባ ዲዛይን፡** በጨረቃ ምሽት ያሉ ዕጽዋት እና ከናታን አልተርማን ግጥም፣ "ሺር ቦኬር" ውስጥ የተወሰኑ መስመሮች።
- **ለዓይነ ስውራን የሚረዱ ምልክቶች፡** በገንዘብ ኖቱ ህዳግ በታችኛው ክፍል ከግራ ወደ ቀኝ የተቀመጡ አራት ጥንድ መስመሮች።
- **የሼቄል ኖቱ የሚለቀቅበት ጊዜ፡** ታኅሣሥ (ዲሴምበር) 2015።

አዲሱ ባለ50 ሼቄል ኖት

- **ምስል፡** ሻኡል ቲሽሬኒሖቪስኪ
- **ዋናው ደማቁ ቀለም፡** አረንጓዴ

- **መጠን፡** 136 x 71 ሚሊ ሜትር
- **የፊት ለፊት ዲዛይን፡** የገጣሚው ምስል በኮምጤ ዛፍና ፍሬዎቹ መደብ ላይ ይታያል።
- **የጀርባ ዲዛይን፡** መደቡ የኮርኒቲያን ምሰሶ እና ከሻኡል ቲሽሬኒሖቪስኪ ግጥም፣ "አኒ ማእሚን" ውስጥ የተወሰኑ መስመሮች።
- **ለዓይነ ስውራን የሚረዱ ምልክቶች፡** በገንዘብ ኖቱ ህዳግ በታችኛው ክፍል ከግራ ወደ ቀኝ የተቀመጡ ሁለት ጥንድ መስመሮች።
- **የሼቄል ኖቱ የሚለቀቅበት ጊዜ፡** መስከረም (ሴፕቴምበር) 2014።